# COVID-19 የቤት ኪራይ ድጎማ ገንዘብ እርዳታ (Rent Relief Grants) ሁለተኛ ዙር/Round Two

ጥያቄዎችና መልሶች

AMHARIC
አማርኛ

**ህጋዊ**

## Rent Relief Grant ምንድ ነው?

ሰዎች የራሳቸውን ቤት እንዲከራዩ የቪክቶሪያ መንግሥት ለቤት ኪራይ ድጎማ የሚሆን ገንዘብ እርዳታ አቀናጅቷል። በ2021 ቀደም ሲል የሚያበቃ ተመሳሳይ መርሀ ግብር የቪክቶሪያ መንግሥት አካሄደ።

የገንዘብ እርዳታው የሚቀርበው በኮሮናቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ ምክንያት የገቢ ምንጭ ላጡ ቪክቶሪያውያን ሲሆን ይህም ለቤት ኪራይ መክፈል ችግር ላለባቸው ቪክቶሪያውያን እስከ $1,500 ሊፈቀድላቸው ይችል ይሆናል።

## ለ Rent Relief Grant ማነው የሚፈቀድለት?

ለገንዘብ እርዳታው ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለብዎት:

- ከእርስዎ አከራይ ባለንብረት ጋር ለቤት ኪራይ ቅነሳ ስምምነት ማድረግ እና ከህጋዊ ጽሁፋዊ ማረጋገጫ ጋር ማስረጃ ማቅረብ
- በየሳምንት የሚያገኙት የገቢ መጠን ከ $1,208.85 በታች (እንደ ብቸኛ ሰው) ወይም $1,813.46 (እንደ ባለትዳር መሆን)
- ከሚያገኙት ገቢ መጠን ከመቶ 30% እጅ በላይ የሚሆን ለባለንብረቱ የቤት ኪራይ የሚከፍሉ ሲሆኑ
- የተቀመጠ ገንዘብ ከ $2,000 በታች ከሆነ

ለአመልካቾች የዜግነት ወይም የቋሚ ነዋሪነት መሆን አያስፈልግም።

## ለገንዘብ እርዳታው እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ለ Rent Relief Grant በኦንላይ በድረገጽ <https://rentrelief.covid19.dhhs.vic.gov.au/>.ማመልከት ይችላሉ

## የገንዘብ እርዳታውን ለምን መጠቀም ይቻላል?

የገንዘብ እርዳታው ከተፈቀደልዎት፤ ክፍያው በቀጥታ ለእርስዎ ባለንብረት ይሰጣል፤ ይህም እንደ የእርስዎ ቤት ኪራይ የሚከፈል ዕዳ ወይም የወደፊት ቤት ኪራይ ውል ክፍያዎች እንዲሆን የተከፈለ ተቀማጭ ገንዘብ ይሆናል።

## ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ወቅታዊ ለሆነ መረጃ በCOVID-19 Rent Relief Grants ድረገጽ
<https://www.housing.vic.gov.au/help-renting/rentrelief> ላይ ማየት

ከዚህ በላይ ላሉት የሆነ መረጃ የአስተርጓሚ እርዳታ ካስፈለግዎት ለትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (Translating and Interpreting Service) (TIS አገር አቀፍ) ስልክ 131 450 ይደውሉ።

በቪክቶሪያ መንግሥት ፈቃድ የታተመ። አድራሻ: 1 Treasury Place, Melbourne.

© ቪክቶሪያ ክፍለ-ሃገር፣ አውስትራሊያ፣ Department of Families, Fairness and Housing። ጥቅምት/October 2021.